ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የዘንድሮ የትምህርት ጅማሮ

**እየሩስ ተስፋዬ**

የመንግሥትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶች በእረፍት ላይ የነበሩትን ተማሪዎቻቸውን ለመቀበል በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ሲሠሩ እንደነበር ይታወቃል። ትምህርት ቤቶችን ማስዋብና ማደስ፣ መምህራንን ማሰልጠን፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከል መምህራን እንዲከተቡ ማድረግ እና ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን መገንባት ከቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መካከል ይጠቀሳሉ። እንዲሁም አቅም የሌላቸውን ተማሪዎች ለመደገፍ በመንግሥት፣ በባለሀብቶች፣ በግብረ ሠናይ ድርጅቶች እና በተለያዩ በጎ ፈቃደኛ ግለሰቦች ተሳትፎ አድርገዋል። ተማሪዎቹ ከትምህርት ገበታቸው እንዳይገለሉ ለማድረግ፤ አገሪቱም በእውቀት የበለጸገ ችግሮቿን የሚፈታላት ትውልድ እንድታፈራ ለማስቻል የተለያዩ የመማሪያ ቁሳቁሶችን በመደገፍ፤ የትምህርቱ ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆን በርካቶች የሚያስመስግናቸውን ሥራ ሠርተዋል።

ትምህርት ከመጀመሩ በፊትም የጤና ሚኒስቴር በሰጠው መግለጫ ላይ አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለመከላከል መምህራን ክትባት እንዲወስዱ፣ መምህራን እና ተማሪዎችም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደረጉ ማሳሰቡም የሚዘነጋ አይደለም። በትምህርት ቤቶች ውስጥ አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዲደረግም ተጠይቋል።

ከነዚህ የቅድመ ሥራዎች ጎን ለጎንም የዘንድሮ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተጀምሯል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2014 የትምህርት ዘመን በከተማ ደረጃ ጥቅምት 01 ቀን 2014 በይፋ ጀምሯል። ይህንን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በቂርቆስ ክፍለከተማ አዲስ ምዕራፍ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገኝተው ለተማሪዎቸ መልዕክታቸውንም አስተላልፈዋል። ‹‹ኢትዮጵያ የእናንተን በሰላም ማደግ፤ በእውቀት መታነጽ በጉጉት የምትጠብቅ እና ለዚህም ጥረት የምታደርግ ሀገር ናት። እናንተም ለዚሁ አላማ አገራችሁን የምትወዱ ለአገራችሁ ጥሩ መሪ እንድትሆኑ የምትዘጋጁ እና የተለያየ ዘርፍ ላይ ተሰማርታችሁ ውጤታማ ሥራ እንድትሰሩ እንዲሁም አገራችሁን እንድታሳድጉ በርትታችሁ እንድታጠኑ፣ በሥነምግባር የታነጻችሁ እንድትሆኑን አደራ እላለሁ›› ብለዋል።

አክለውም ‹‹መምህራንም የድካማቸውን እና የልፋታቸውን ውጤት እንዲያዩ እና በአዲሱ ዓመት አዲስ እውቀት ለማስጨበጥ ስላደረጋችሁት ዝግጅት ሁሉ ምስጋና ይገባችኋል።›› በማለት ከንቲባዋ ምስጋናቸውን ችረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ በበኩላቸው በ2014 የትምህርት ዘመን በአዲስ አበባ ከተማ ከ910ሺህ በላይ ተማሪዎች ምዝገባ መካሄዱን ጠቅሰው፤ በትምህርት ዘመኑም በከተማዋ ለሚገኙ ከ600ሺህ በላይ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች የምገባ መርሃ ግብሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ መርሃ ግብሩ በይፋ መጀመሩን እና ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል። የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያም ሠፊ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመዋል።

በዕለቱም የትምህርት ግብዓት ቁሳቁስ መርሐግብር የተከናወነ ሲሆን በከንቲባዋ አማካኝነት ለተማሪዎች ቦርሳ፣ ደብተር፣ የደንብ ልብስ(ዩኒፎርም) እና መሰል ግብዓቶች በማበርከት የትምህርት መርሃግብሩ በይፋ ተጀምሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ጅማሮን ቂርቆስ ክፍለ ከተማ በሚገኙት ኡራኤል አንደኛ ደረጃ እና ምሥራቅ ጎህ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገኝተው ምልከታ አድርገዋል። በመስክ ምልከታው ወቅት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት አስተያየት የትምህርት ዓመቱ በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች መጀመሩንና ለዚህም ይረዳ ዘንድ ባለፉት ሁለት ወራት የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ሲሰሩ እንደነበር ገልጸዋል። በመስክ ምልከታው ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ለኮቪድ ተጋላጭ እንዳይሆኑ ከማስቻል አንጻር መምህራንና ሌሎች የትምህርት አመራሮችም ቀደም ብለው የኮቪድ ክትባት እንዲወስዱ መደረጉን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም የትምህርት መርሃግብር በይፋ ካስጀመሩት ክልሎች ውስጥ የኦሮሚያ ክልል ይጠቀሳል። በክልሉ የመማር ማስተማር ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን መግለጻችን ይታወሳል። ለአብነትም የተማሪዎች ምዝገባ ማካሄድ፣ ትምህርት ቤቶችን ማስዋብ እና ማደስ እንዲሁም መምህራን ማስከተብ፣ ማሰልጠን እና መቅጠርን ይመለከታል። ኮቪድን ከመከላከል ረገድም ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን መገንባታቸውም ይታወቃል።

በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ፤ በቢሾፍቱ «ከራ ሆራ መዋለ ሕፃናት እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት» በመገኘት የ2014 ዓ.ም የመማር ማስተማር ሂደት በይፋ መጀመሩን በማብሰር፤ በክልሉ ከ9 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ትምህርት ለመጀመር መመዝገባቸው ተነግሯል።

ዶክተር ቶላ እንደገለፁት፤ የመማር ማስተማር ሂደቱ የኮሮና ቫይረስ መከላከል ፕሮቶኮል (መመሪያ) ያከበረና ተማሪዎች በኮቪድ 19 እንዳይያዙ ጥንቃቄን መሠረት ባደረገ መልኩ እንደሚካሄድም በመጥቀስ፤ በክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የንጽህና አገልግሎት ለማሟላት በተደረገው እንቅስቃሴ የኢፋ ቦሩና ቡኡ’ራ ቦሩ ትምህርት ቤቶች በባለሀብቱ እና በመንግሥት ትብብር ተጠቃሚ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በክልል እየተገነቡ ከሚገኙ ሦስት ሺህ የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ሺህ ትምህርት ቤቶች ማጠናቀቅ ተችሏል። ለትምህርት ቤቶቹ የትምህርት መሣሪያዎች እና ቁሳቁሶች የተሟላላቸው ሲሆን፣ የትምህርት ቤቶችን የተማሪዎች ቁጥር እና የመማሪያ ክፍሎችን መጠን (ስፋት) ግምት ውስጥ በማስገባት ርቀታቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲሁም አስገዳጅ ከሆነም የፈረቃ ሥርዓትን በመተግበር የመማር ማስተማር ሒደቱ እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

በአጠቃላይ የዘንድሮው የትምህርት ዘመን እና የትምህርቱ ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆን ተማሪዎችም ጤንነታቸው ተጠብቆ፤ ራሳቸውንም ከዚህ ወረርሽኝ ለመከላከል በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጪ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል። ወረርሽኙን ለመከላከል ይረዳ ዘንድም መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች እና ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር
በመተባበር በየ15 ቀኑ ዓርብ የሚታተም

# ‹‹ሁሌም አርአያ የሚሆን ቀዳሚ ድርጅት ነው››

ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር







ሽልማት የትጋትና የጥረት ውጤት ነው። ያለልፋትና ያለድካም የሚሰጥ ሽልማት የለም። ሰርቶ ደክሞ ጥሮና ግሮ ለሽልማት መብቃት ለተሸላሚው ብቻ ሳይሆን በተሸላሚው ዙሪያ ላሉ አካላት ደስታው ይደርሳል። ድርጅታችን የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በቀን ከመቶ ሺህ ሰው በላይ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል። ይህን ያህል ሰው እያስተናገዱ በአገልግሎት አሰጣጥ የጥራት ተሸላሚ መሆን ቢከብድም ድርጅቱ አሳክቶታል። በጣም ደስተኛ ነኝ። ድርጅቱ የሚኒስትራችን ተጠሪ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ውጤቱ የኛም ነው ብለን ወስደን ተደስተናል። የድርጅቱ አመራርና ሠራተኞች ቅንጅት ውጤት ነው። ያለዕረፍት በሚሰራ ሥራ የሚገኝ ድል ነው።

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ሁሌም አርአያ የሚሆን ቀዳሚ ድርጅት ነው። እንደሚኒስትሪ የሰጠነውን የሥራ አቅጣጫ ሰርቶ ማስረከብ ብቻ ሳይሆን ልዩ ፈጠራና ፍጥነት ጨምሮ ተቆጥሮ የተሰጠውን ሥራ እሴት ጨምሮ የሚያስረክብ ዘርፋችን ምርጥ ተቋም መሆኑን እመሰክራለሁ። ለውጥ ሁልጊዜም አዳጊ ስለሆነ ከዚህ የበለጠ መስራት አለባችሁ ብዬ አምናለሁ። በተገኘው ውጤት ተበረታታችሁ በአንደኛ ደረጃ ተሸላሚ ለመሆን መትጋት ይጠበቅባችኋል። በተረፈ ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ሁሌም በተቋሙ ደስተኛ ነው። የሚጠበቅብንን ደግፈናል፤ በቀጣይ ድጋፋችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።

2014 የሰላምና የብልፅግና እንዲሆን እመኛለሁ።

**(ከድርጅቱ ዓመታዊ መጽሄት የተወሰደ)**